# ADDA BILISUMMAA OROMOO

OROMO LIBERATION FRONT

جبهة تحرير أورومـــو

Gaafa: 10-12-2012 تاريخ
Date:

Lakk.: 004/xal-abo/2012 رقم
No.:

## በኦሮሞ ህዝብ የነፃነት ትግል ሂደት ላይ ግራ መጋባትን ለመፍጠር የሚደረግ ጥረት ተሳክቶ ኣያውቅም

### *የኦሮሞ ነፃነት ግንባር መግለጫ*

የወያኔ መንግስት በስርኣቱ ላይ የሚካሄደውን፣ በተለይም በኦሮምያ እየተፋፋመ ያለውን የኦነግ እንቅስቃሴና የህዝቡን ኣንገዛም ባይነት ኣመፅ ለማፈን ቢጥርም እየተሳካለት ኣይደለም። ገመናውን የሸፋፈኑለት የውጭ ወዳጆቹም የስርኣቱን ቁስል ለማዳን መረባረባቸው ተደጋግሞ ተስተውሏል። በተለይም ባለፉት ስድስት ወራት የወያኔ መንግስት ይበልጥ በኦነግ እንቅስቃሴና በኦሮምያ እየተስፋፋ ባለው ህዝባዊ ኣመፅ ኣጣብቂኝ ውስጥ ገብቷል። ከዚህም የተነሳ እስከ ዛሬ ድረስ ሲጠቀምባቸው የቆየውን ያረጁና ኣሰልቺ የማደናገሪያ ስልቶቹን ለመደጋገም ቢገደድም ጥረቶቹ ዛሬም ሆነ ነገ ሊሳኩለት እንደማይችሉ እናስገነዝባለን።

የህወሃት/ኢህኣዴግ ስርኣት ከገባበት ኣጣብቂኝ ራሱን ለማውጣት ሲል እንደ ዋና ኣማራጭ የታየው ነገር ቢኖር የኦሮሞ ነፃነት ግንባርን ቢቻል ማፍረስ ካልተቻለም ለማዳከም መጣር ነው። ከዚሁ ጎን ለጎን ደግሞ *ሰላማዊ ድርድር፣ ኮንፈረንስ፣ ሽምግልና* የተሰኙና የመሳሰሉትን የተለመዱ ስልቶቹን በመጠቀም የኦነግ ታጋዮችን ከፋፍሎ እርስ በርስ ለማቃቃር መሞከር ነው። ባለፉት ሃያ ኣመታት ሙሉ ይህንን ድርጅት ከውጭ እየወጋው ማሸነፍ ስላቃተው ከተቻለለት እጁን ኣስገብቶ ውስጣዊ ችግሮችን ፈጥሮ ማተራመስን ኣቅዶ እየሰራ ቆይቷል። የኦነግን ድርጅታዊ ኣንድነት ለመናድ ሲል በስመ እርቅ ኣሳብቦ የተወሰኑትን የድርጅቱ ኣባላት ማርኮ ከእጁ ለማስገባትም ይመኛል። በኦነግነት ራሳቸውን የሚጠሩ ኣልያም ሌላ ኣዲስ ስም ያወጡ ስብስቦችን በድርጅትነት ጠፍጥፎ የኦሮሞ ህዝብን ቅስም ለመስበርና የህዝቡን ሃይል ለመበታተን ያልማል።

በስልጣን ላይ ያለው ጠላት ይህንን ኣፍራሽ ኣላማውን ለማሳካት በሚያደርገው ጥረት ለራሳቸውም ሆነ ለህዝባቸው ክብር የሌላቸውን ጥቂት ወገኖች ኣሰባስቦ እንደ መሳሪያ ሲጠቀምባቸው ቆይቷል። በተለይም ኦነግን ከህዝብ ለመነጠል ያልወጣው ዳገትና ያልወረደው ቁልቁለት ኣልነበረም። ይሁንና ታዲያ ኣልተሳካለትም። ኣንድ ቀላል ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል፣ ወያኔ ኦነግን ከሽግግር መንግስቱ ገፍቶት ባስወጣው ማግስት "*ሰላማዊ ኦነግ*" ብሎ ኣንድ ስብስብ በድርጅትነት ጠፍጥፎ የኦሮሞን ህዝብ ሊያታልልበት ሞክሮ ነበር። ይሁን እንጂ ህዝባችን የማወናበጃ ስልቱን ወዲያው ነቅቶበት የወያኔውን ጥፍጥፍ *ሰላማዊ ኦነግ* ተብዬ ተቀባይነት ኣሳጣው። ባሁኑ ወቅትም በኦነግና ኣመራሩ ላይ ኣፍራሽ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ በመክፈትና በማስከፈት በኦሮሞ ህዝብ ትግል ጎራ ውስጥ ትርምስና ግራ መጋባት እንዲፈጠር የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም። እንቅልፍ የነሳውን የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ለማዳከም ካለው ፅኑ ምኞት በመነሳት ሌላ ኣዲስ ድርጅት ለመጠፍጠፍ ወይም ለማስጠፍጠፍ እያደባ መሆኑ ይታያል። የኦሮሞ ህዝብ የነፃነት ትግል ጎራ እየጠራ ባለበትና ቀደም ሲል በኣፍራሽ ፕሮፓጋንዳዎች ተደናግረው የቆዩ ወገኖች ኣሁን ሃቅን ከውሸት ለይተው በመረዳት ወደ ድርጅታቸው ለመመለስ እየተንቀሳቀሱ ባሉበት በዚህ ወቅት ጠላት ሌላ ኣፍራሽ ጥረት ማድረጉ ሊያስገርም ኣይገባም። ጠላት መቼም ጠላት ነውና የኦሮሞ ልጆች ኣንድነት ሲያንሰራራ ማየት ያሳስበዋል።

P. O. Box 6973 Asmara, Eritrea | Telefax 291 1 110236 | E-mail abamilki@gemel.com.er

በዚህ ጉዳይ ላይ ሃገር ቤትና በውጪው ኣለም ለሚኖረው የተከበረው ሰፊ ህዝባችን
ሁለት ታላላቅ መልእክቶችን ማስተላለፍ እንወዳለን። የመጀመሪያው፥ ኣዲስ ድርጅት
ለመጠፍጠፍ የሚደረገውን ጥረት የሚመለከት ይሆናል። የኦሮሞ ህዝብ ትግል ችግር የ
ፖለቲካ ድርጅቶች ቁጥር ከማነሱ የሚመነጭ ኣይደለም። ኦነግ ከተመሰረተበት ዘመን
ኣንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ በተለያዩ ስሞች የሚጠሩ ኣዳዲስ ድርጅቶች ሲመሰረቱ
ቆይተዋል። ነገር ግን ለትግሉ ስኬታማነት የሚያግዙ የሰው ሃይል፥ ኢኮኖሚ፥ ጊዜና
እውቀትን በከንቱ ከማባከን ውጪ በነዚህ የግንጠላና የጥፍጠፋ ተግባራት ሁሉ የተገኘ
ኣንድም ገንቢ ውጤት ኣልታየም።

ነገም ቢሆን ኣዲስ ድርጅት ለመጠፍጠፍ ወይም ከኦነግ ላይ የተወሰነውን ኣካል
ለመገንጠል መጣር ማለት የወያኔን ፍላጎት ለማሳካት ማገዝ ካልሆነ በስተቀር ለኦሮሞ
ህዝብ ትግል ምንም የሚያመጣው መፍትሄ ኣይኖርም። መፍትሄ ሊሆን የሚችለው
እልፍ ኣእላፍ የኦሮሞ ልጆች የተሰውለትን ድርጅት ኣጠናክሮ የታጋይነትና የዜግነት
ድርሻን በብቃት መወጣት ብቻ መሆኑን ማስታወስ እንወዳለን። ስለሆነም ህዝባችን፥
በተለይም ደግሞ ሃገር ቤትና በውጪው ኣለም የሚገኙ የድርጅቱ ታጋዮች በድርጅ
ታቸው ላይ እየተቃጣ ያለውን የጥቃት ሴራ እየመከቱ በወያኔ መንግስት ላይ የተያ
ያዙትን ትግል እንዲያፋፍሙ ጥሪ እናቀርባለን።

የወያኔ መንግስት በስርኣቱ ላይ ያነጣጠረ የትግል እንቅስቃሴ ባየለበት ቁጥር መሰረት
የሌለው የውሸት ድርድር እያራገበ ከተቻለለት በኦነግ የሚመራውን ትግል ሙሉ
በሙሉ በቁጥጥሩ ስር ለማስገባት ያልማል። ካልተቻለለትም ደግሞ የህዝቡንና የድርጅ
ቱን ደጋፊዎች ቀልብ በማማለል በመካከላቸው ክፍፍልን ለመፍጠር ይመኛል። ይህን
ምኞቱን እውን ለማድረግ ባለፉት ሃያ ኣመታት ሙሉ ጥሯል፥ ዛሬም ከዚህ ጥረቱ ኣ
ልተቆጠበም። ከወያኔ መንግስት ጋር ሊካሄድ ስለሚችል ድርድር በተመለከተ ኦነግ የሚ
ከተለውን ቋሚ ፖሊሲውን መልሶ መላልሶ ማስታወስ ይወዳል። ይሄውም፥ የወያኔ
መንግስት ለኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ በቀና መንፈስ ሰላማዊ ምላሽ ለመስጠት ከፈለገ
ያለምንም ድብብቆሽ ለሰፊው ህዝብና ለኣለም ህብረተሰብ ክፍት በሆነበት ሁኔታ በኣ
ለም ኣቀፍ ደረጃ እውቅና ያለው ሶስተኛ ወገን በተገኘበት ሶስተኛ ሃገር ውስጥ
ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለመደራደር ዝግጁ መሆኑን ኦነግ ያስገነዝባል። ከዚህ ውጪ
በኮንፈረንስ፥ በሽምግልናና በመሳሰሉት ማደናገሪያ ስልቶች ስልጣን ላይ ባለው መንግስ
ት ገፋፊነት የሚደረጉ ፍሬቢስ ጥረቶች ከቶውንም ተቀባይነት እንደሌላቸው ማስገንዘብ
እንወዳለን።

ጠቅለል ባለ መልኩ በኦሮሞ ነፃነት ሰራዊት፥ በኣባሎቻችንና በህዝባችን እየተካሄደ
ባለው ይትግል ሂደት ላይ ግራ መጋባትን ለመፍጠር በማንኛውም መልኩ የሚደረግ
ጥረት እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ በህዝቡ ትግል የሚከሽፍ መሆኑን ኣበክረን እናስገነዘ
ባለን።

*ድል ለኦሮሞ ህዝብ!*

*የኦሮሞ ነፃነት ግንባር*

*ማርች 10, 2012*